በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የቦሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የ፲፱፻፲፭ ዓ.ም

የ፰ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሞዴል ፈተና

የጥያቄ ብዛት፡- ፶ የተፈቀደው ሰዓት፡- ፪ ሰዓት

አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ ፶ ጥያቄዎች ተካተዋል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል። በፈተና ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መሥራት ይጠበቅባችኋል። መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው። በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛው መልስ የሚጠቁረው በእርሳስ ብቻ ነው። ትክክለኛውን መልስ ለማጥቆር ሚሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት። የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት።

ፈተናውን ሠርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰዓት ፪ ሰዓት ነው። ፈተናውን ሠርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመሥሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥና ፈተናውን መሥራት ማቆም አለብን። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን።

የሚኮርጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል።

ፈተናውን መሥራት ከመጀመራችሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባው መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት።

ፈተናውን ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም!

መመሪያ አንድ፡- ከተራ ቁጥር ፩ እስከ ፭ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ምንባቡን በጥሞና በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ።

<u>ምንባብ</u>

ደራሲ በዓሉ ግርማ በኢሳባቡር ክፍለ ሀገር ሱጴ በምትባል ሥፍራ በ 1932 ዓ.ም. ተወለዱ። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በልዕልት ዘነበወርቅ ትምሕርት ቤት ፤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በጄኔራል ዊንጌት ትምህርት ቤት አጠናቀዋል። ከዚያም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፖሊቲካል ሳይንስ እና ኢንተርናሽናል ሪሌሽንስ የ ቢ.ኤ. ዲግሪ ያገኙ ሲሆን፤ በዚሁ ተመሳሳይ መስክ ከአውሮፓ በ 1955 ዓ.ም የማስተርስ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል።

ደራሲ በዓሉ ግርማ በተለይ በልብ ወለድ እና በፈጠራ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ከታወቁት የኢትዮጵያ የዘመኑ ደራሲዎች መካከል ተወዳጅነትና ዝናን ያተረፉ ዕውቅ ደራሲ ነበሩ። ከጻፏቸው በርካታ ድርሰቶቻቸው ውስጥ «ከአድማስ ባሻገር» የተሰኘው የመጀመሪያ መጽሐፋቸውን በ 1962

ዓ.ም አሳትመዋል። ይህ መጽሐፋቸው በሩስያኛ ቋንቋ ተተርጉሞ በቀድሞዋ የሶቪየት ሶሽያሊስት ሪፑብሊኮች ኅብረት ቀርቧል። ሌሎች ልቦለዶችን የጻፉ ሲሆን የቀይ ኮከብ ጥሪ፣ የህሊና ደውል፣ ደራሲው እና ሀዲስ የተሰኙትን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

ደራሲው በጋዜጠኝነት ሙያም ስማቸውን ያስጠሩ፤ ሙያቸውንም ያስከበሩ ደራሲ ነበሩ። «የዛሬይቱ ኢትዮጵያ» ጋዜጣ በማዘጋጀት ከ 1955-1957 ድረስ ሰርተዋል፤ የመነን መጽሔት ከ 1958 እስከ 1960 ዓ.ም ሰርተዋል፤ የአዲስ ሪፖርተር መጽሔት ከ 1957 እስከ 1958 በአዘጋጅነት ሰርተዋል ፤ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከ 1962 እስከ 1966 ድረስ ዋና አዘጋጅ በመሆን ከመሥራታቸውም ባሻገር፤ ብዙ ወጣት ጋዜጦችን ለማፍራት ጥረት አድርገዋል። አዲስ ሪፖርተር የተባለውን መጽሔትም ደረጃው ከፍ እንዲልና በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲገመገም አድርገዋል። በጋዜጠኝነት ሙያቸው በኢትዮጵያ ራዲዮ ሠርተዋል።

ደራሲ በዓሉ ግርማ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱና ብዙ ሥራዎችን ያቀረቡ ሲሆን፤ የመጨረሻው መጽሐፋቸው በ 1972 ዓ.ም የታተመው መጽሐፋቸው «ኦሮማይ» በመባል ይታወቃል። ይኼውም መጽሐፍ በወቅቱ በነበረው የደርግ መንግሥት ሊደገፍ ባለመቻሉ በ 1976 ዓ.ም. ለደራሲው ሕይወት መጥፋት መንስኤ ሊሆን በቅቷል።

ምንጭ፦ ሀብታሙ ግርማ ።2011 ዓ.ም ስለየስነጽሑፍ ሰዎች እና ስራዎቻቸው። አ.አ ፣ኢምፕረስ ማተሚያ ቤት፣ከገጽ 240 እስከ 243 በመጠኑ ተሻሽሎ የቀረበ

፩. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ በዓሉ ግርማ የህይወት ታሪክ ትክክል የሆነው የትኛው አረፍተ ነገር ነው?

A. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በልዕልት ዘነብወርቅ ትምህርትቤት ተምረዋል።

B. በ 1932 ዓ.ም በኢሉባቦር ሱጴ በተባለች መንደር ተወለዱ።

C. በደራሲነት ብቻ የህይወት ዘመናቸውን ፈጅተዋል።

D. የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በቋንቋ እና ስነጽሑፍ አግኝተዋል።

፪. ደራሲ በዓሉ ግርማ የማስተርስ ዲግሪያቸውን በየትኛው ዓመተምህረት አገኙ?

A.1932 ዓ.ም B.1955 ዓ.ም

C.1962 ዓ.ም D. 1972 ዓ.ም

፫. የደራሲ በዓሉ ግርማ የመጀመሪያ መጽሐፋቸው የሆነው የትኛው ነው?

A. ኦሮማይ B. የቀይ ኮከብ ጥሪ

C. የህሊና ደውል D. ከአድማስ ባሻገር

፬. ከደራሲው መጻህፍት ውስጥ ወደ ሩሲያኛ ቋንቋ የተተረጎመው የትኛው መጽህፍ ነው?

A. ኦሮማይ B. የሕሊና ደውል

C. ከአድማስ ባሻገር D.ሐዲስ

፭. ስለጋዜጠኝነት ስራቸው የሚገልጸው አንቀጽ የትኛው ነው?

A. የመጀመሪያው አንቀጽ B. ሦስተኛው አንቀጽ

C. ሁለተኛው አንቀጽ D. አራተኛው አንቀጽ

፮. በሁለተኛው አንቀጽ የመጨረሻው አረፍተ ነገር ላይ "ለአብነት" የሚለውን ቃል ሊተካ የሚችለው የትኛው አማራጭ ነው?

A. ለአርአያነት B. ለምሳሌነት

C. ለአባትነት D. ለወዳጅነት

፯. በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ በቆዩበት ወቅት ረጅም ጊዜ ወስደው የሰሩት በየትኛው ጋዜጣ ወይም መጽሄት ላይ ነው?

A. አዲስ ዘመን ጋዜጣ B. የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ

C. አዲስ ሪፖርተር ጋዜጣ D. መነን መጽሄት

መመሪያ ሁለት፦ ከጥያቄ ቁጥር 8 እስከ $5 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

፰. ሰውየው ጥቂት ካጣጣረ በኋላ <u>አረፈ።</u> በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ዓውዳዊ ፍቺ ሊሆን የሚችለው የትኛው አማራጭ ነው?

A. ተጠንቅቆ ቆመ B. ሞተ

C. እረፍት ወሰደ D. ተኛ

፱. መሃመድ እና አበበ በሬዎቻቸውን <u>አቀናጅተው</u> ለማረስ ተስማሙ። በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቺ ሊሆን የሚችለው የትኛው አማራጭ ነው?

A. አጣምረው B. ለያይተው

C. አርደው D.ነጣጥለው

፲. <<አዛባ>> የሚለው ቃል ጠብቆ ሲነበብ የትኛውን ትርጉም ይሰጣል?

A. ረኸጥ B. የላቀጠ ጭቃ

C. የላቀጠ እበት D. ፍርደ ገምድል

፲፩. <<ተልባ>> ለሚለው ቃል ፍካሬያዊ ፍቺ ሊሆን የሚችለው የትኛው አማራጭ ነው?

A. የቅባት እህል B. ጥራጥሬ C.የማይጨበጥ D. ቁም ነገረኛ

፲፪. ከሚከተሉጥ አማራጮች መካከል ልዩ የሆነው ቃል የትኛው ነው?

A. ባዝራ B. ቄብ

C. ጊደር D. ኮረዳ

፲፫. ከሚከተሉት ውስጥ የክርክር ዝግጅት መመሪያ ያልሆነው የትኛው ነው?

A. መረጃ መሰብሰብ B.ሃሳብን ቅደም ተከተል ማስያዝ

C. ስብዕናን አሟልቶ መገኘት D. .ሃሳብን በቅደም ተከተል ማቅረብ

፲፬. ከሚከተሉት ውስጥ የውይይት አቀራረብ መመሪያ የሆነው የቱ ነው?

A. ሐሳብን በማስረጃ አስደግፎ ማቅረብ B. መረጃ መሰብሰብ

C. ርዕሰ ጉዳዩን በደንብ መረዳት D. መረጃን ማደራጀት

፲፭. ከሚከተሉት ውስጥ በገጠመኝ ላይ ተመስርቶ ሊካሄድ የሚችለው የትኛው ነው?

A. ክርክር B. ውይይት

C. ቄውውት D. ድርድር

፲፮. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የቢጋር ጥቅም ያልሆነው የትኛው ነው?

A. የሃሰብ ቅንጅትን ለማየት B. ከርዕሰ ጉዳይ ላለመውጣት

C. ዓላማን ግልጽ ለማድረግ D. ርዕሱን አጥብቦ ለመወሰን

፲፯. ድርሰት ከመጻፋችን በፊት የምንከተላቸው ሂደቶች በቅደም ተከተል ሲቀመጡ የትኛውን አማራጭ ይይዛሉ?

A. ርዕስ ማጥበብ፣ ቢጋር ማዘጋጀት፣ርዕስ መምረጥ፣ረቂቅ መጻፍ

B. ርዕስ መምረጥ ፣ርዕስ ማጥበብ፣ ቢጋር ማዘጋጀት፣ ረቂቅ መጻፍ

C. ቢጋር ማዘጋጀት፣ ርዕስ መምረጥ፣ ርዕስ ማጥበብ፣ ረቂቅ መጻፍ

D. ርዕስ ማጥበብ፣ ርዕስ መምረጥ ፣ቢጋር ማዘጋጀት ፣ ረቂቅ መጻፍ

፲፰. አንድ ሰው የሌላን ሰው ታሪክ ቢጽፍ ከየትኛው የህይወት ታሪክ ይመደባል?

A. ግለ ታሪክ B. የታዋቂ ሰው ታሪክ

C. የህይወት ታሪክ D. የራስ ታሪክ

፲፱. ከሚከተሉት ውስጥ ከአጭር ልቦለድ ባህርያት የማይመደበው የትኛው ነው?

A. ጥድፊያ B. ነጠላ ውጤት

C. ውስን መቼት D. ገጸባህርይ

፳. ከልቦለድ ማቅረቢያ ዘዴዎች ውስጥ ያለፈውን አሁን ላይ መተረክ ምልሰት ከተባለ ወደፊት የሚሆነውን አሁን መናገር----------ይባላል?

A. ራዕይ B. ገለጻ

C. ንግር D. ትልም

፳፩. ከሚከተሉት መካከል ልዩ የሆነው የትኛው ነው?

A. መቼት B. ገለጻ

C. ትልም D. ገጸባህርይ

፳፪. ከሚከተሉት ውስጥ ስለልቦለድ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

A. ድርሰት መጻፍ የፈለገ ሁሉ ይጽፈዋል።

B. በመረጃ የተደገፈ መሆን አይጠበቅበትም።

C. ገጠመኝን መነሻ በማደረግ የሚጻፍ የፈጠራ ጽሁፍ ነው።

D. የቃላት ማፈንገጥ እና ማጋነንን ይፈቅዳል።

፳፫. ከቋንቋ መዋቅር አንጻር ቀዳሚ የሆነው የቱ ነው?

A. ቃል B. ድምጽ

C. ሐረግ D. ምእላድ

፳፬. ስለ ስነቃል ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

A. በመነገር፣በመተረት እና በመዜም ይተላለፋል።

B. የማህበረሰቡ ፍልስፍና ነው።

C. ከጽሁፍ የቀደመ ሃብት ነው።

D. በጽሁፍ የሚተላለፍ ነው።

፳፭. ከሚከተሉት የስነቃል አይነቶች ውስጥ ልዩ የሆነው የቱ ነው?

A. ተረት B. አፈታሪክ

C. ሀተታ ተፈጥሮ D. ሙሾ

፳፮. በቃለ ጉባኤ አያያዝ ወቅት የማይካተት የትኛው ነው?

A. አጀንዳዎቹን መጻፍ B. ቀንና ዓመተምህረት መጻፍ

C. የተገኙ እና ያልተገኙ አባላት መጻፍ D. የተሳታፊዎችን ሃሳብ አስፋፍቶ መጻፍ

፭፯. ‹‹ስለአስፈላጊነታቸው›› የሚለው በምእላድ ተተንትኖ ሲጻፍ የትኛው አማራጭ ትክክል ይሆናል?

A. ስለ-አስፈላጊ-ነት-ኣቸው B. ስለ-አሰ-ፈላጊ-ነት-ኣቸው

C. ስለ-አሰ-ፈላጊነት-ኣቸው D. ስለ-አስፈላጊነት-ኣቸው

፭፰. ‹‹አስቀጠቀጥኩት›› በሚለው ቃል ውስጥ የተሳቢ አጸፋ ሊሆን የሚችለው የትኛው አማራጭ ነው?

A. እኔን B. እሱን

C. እኛን D. እነሱን

፭፱. ከሚከተሉት ውስጥ የተሳሳተ ብዜት የተከተለ የትኛው አማራጭ ነው?

A. ሰራዊቶች B. መምህራን

C. እንስሳት D. ገዳማት

፮፬. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች መካከል ትክክለኛውን የትዕምርተ ጥቅስ አጠቃቀም የተከተለ የትኛው ነው?

A. ሰውየው በሃዘኔታ ያን ‹‹ስሜት በስንት ብር፣በምን ያህል ወርቅ›› ገዛኸው ብሎ ጠየቀው።

B. ሰውየው ‹‹በሃዘኔታ ያን ስሜት በስንት ብር፣በምን ያህል ወርቅ ገዛኸው›› ብሎ ጠየቀው።

C. ሰውየው በሃዘኔታ ‹‹ያን ስሜት በስንት ብር፣በምን ያህል ወርቅ ገዛኸው?›› ብሎ ጠየቀው።

D. ሰውየው በሃዘኔታ ‹‹ያን ስሜት በስንት ብር፣በምን ያህል ወርቅ ገዛኸው››? ብሎ ጠየቀው ።

፮፮. ያ ትናንት የገዛሁት ሱሪ ተቀደደ። በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ተውሳከ ግስ ሆኖ የገባው ቃል የትኛው ነው?

A. ያ B. ትናንት

C. የገዛሁት D. ተቀደደ

፮፯. በፈተና ጥሩ ውጤት ለማምጣት ተዘጋጅተን ነበር፤የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እየተፈተንን ነው፤ ጥሩ ውጤትም ይመጣል። እነዚህ አረፍተ ነገሮች በጊዜ ቅደም ተከተል ሲቀመጡ ትክክል የሆነው አማራጭ የትኛው ነው?

A. የአሁን ጊዜ፣የትንቢተ ጊዜ፣የሃላፊ ጊዜ B. የሃላፊ ጊዜ፣የአሁን ጊዜ፣የትንቢት ጊዜ

C. የሃላፊ ጊዜ፣የትንቢት ጊዜ፣የአሁን ጊዜ D. የትንቢት ጊዜ፣የአሁን ጊዜ፣የሃላፊ ጊዜ

፮፰. ከሚከተሉት ውስጥ ሃላፊ ጊዜ ግስ የያዘው አረፍተ ነገር የትኛው ነው?

A. ዘይነባ እያጠናች ነው። B. አስቴርን ትናንትና ታክሲ ውስጥ አየኋት።

C. ነገ እመጣ ይሆናል። D. ምሳዬን ልበላ ነው።

፮፱. በሦስተኛ መደብ ፣ነጠላ ቁጥር ፣ተባዕታይ ጾታ፣ በትንቢት ጊዜ የተነገረው የቱ ነው?

A. ይሄዳል B. ሄዷል

C. ትመጣለች D. ትሄዳለህ

፯፭. ‹‹የጭቃ እሾህ›› ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ተመሳሳይ ፍቺ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

A. በድብቅ ተንኮል የሚሰራ B. ትልቅ እሾህ

C. ቀጥተኛ D. ልግመኛ

፯፮. ትምህርቱን ያቋረጠው ቤተሰብ አልባ በመሆኑ ነው። በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ምክንያት ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

A. ትምህረቱን ያቋረጠው B. ቤተሰብ አልባ በመሆኑ

C. ትምህርቱን ያቋረጠው ቤተሰብ D. እውቀት ስለሌለው

፯፯. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ነጻ ምእላድ የሆነው የቱ ነው?

A. ቀበሌ B. ቤቱ
C. ደሜ D. ልቤ

፴፰. ማንኛውም ስም የሆነ ቃል ተቀጣሪ ነገሮችን የሚጠቁም ከሆነ ምእላዱ ምን ይባላል?

A. የምስረታ ምእላድ B. ነጻ ምእላድ
C. ቅድመ ግንድ ምእላድ D. የእርባታ ምእላድ

፴፱. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል አመዛዛኝ ወይም አወዳዳሪ ድርሰት ለመጻፍ አማራጭ ሊሆን

የሚችለው የቱ ነው?

A. የአዲስ አበባ ነዋሪዎች B. የግል እና የመንግስት ትምህርትቤቶች
C. መምህራን D. ተማሪዎች

፵. የሀረጉ መሪ በግራም ሆነ በቀኝ ሊመጣ የሚችለው በትኛው የሀረግ አይነት ነው?

A. ስማዊ ሀረግ B. ግሳዊ ሀረግ
C. መስተዋድዳዊ ሃረግ D. ቅጽላዊ ሃረግ

፵፩. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ቅጽላዊ ሀረግ የሆነው የትኛው ነው?

A. ለምለም ሳር B. የስንዴ ዳቦ
C. በጣም ደፋር D. ትናንትና ማታ

፵፪. ከሚከተሉት ውስጥ ስማዊ ሃረግ የሆነው የትኛው ነው?

A. የወርቅ ቀለበት B. ያ የአስቴር
C. እጅግ በጣም ታታሪ D. ሰውየው ክፉኛ

፵፫. ሀ. እናቷ በችግር ሲኖሩ ሶስት ልጆች ወልደዋል።

ለ. ጸዳለ አባቷ የሞተባት ገና በህጻንነቷ ነው።

ሐ. አንደኛው አፋን አልፈታምኀ ተከታዩ በእግሩ ድክድክ ይላልኀ የመጨረሻው ገና ከአንቀልባ እድሜ

አልወጣም።

መ. እናቷ እነዚህን ልጆች የሚያስተዳድሩት በልመና ነው።

ከላይ ያሉት አረፍተነገሮች በትክክል ገጣጥሞ አንቀጽ ለመጻፍ የሚሆነው ቅደም ተከተል የቱ ነው?

A. መ፣ሐ፣ለ፣ሀ B. ሀ፣ለ፣መ፣ሐ
C. ሀ፣መ፣ለ፣ሐ D. ለ፣ሀ፣ሐ፣መ

፵፬. ‹‹ቁም ሳጥን መስለህ መጣህ።›› የሚለው አባባል በምን አይነት ዘይቤ የቀረበ ነው?

A. ተለዋጭ ዘይቤ B.ተነጻጻሪ ዘይቤ
C. አያዎ ዘይቤ D. ተምሳሌት ዘይቤ

፵፭. ያ ጥቁሩ አቤል ዛሬ ለምን ወደ ትምህርትቤት አልመጣም? የሚለው አረፍተ ነገር ከአገልግሎት አንጻር

ከየትኛው ይመደባል?

A. ተራ አረፍተ ነገር B. አዎንታዊ መጠይቅ
C. አሉታዊ መጠይቅ D. ውስብስብ አረፍተ ነገር

፵፮. ሽቶዋ ያውዳል ፤ጉራማይሌ የተነቀሱ ጥርሶቿ እንደ እንቁ ያበራሉኀ ከደረቱ ክፍት የሆነ ጥቁር ሹራብ ጣል አድርጋለችኀ የአንገት ጌጧም ደረቷ

ላይ አረፍ ብሏል። ይህ ድርሰት ከየትኛው የድርሰት አይነት ይመደባል?

A. አከራካሪ B. ተራኪ
C. ገላጭ D. ሥዕላዊ

፵፯. የቃሉን የመጨረሻ ሆሄ ወደ ሳብዕ የሚቀይርና ጊዜ አመልካች ቅጥያ በስተመጨረሻ ሊጨምር የሚችለው የቃል ክፍል የትኛው ነው

A. ስም B. መስተዋድድ
C. ተውሳከ ግስ D. ግስ

፵፰. የአቶ አለሙ ሚስት ነፍሰ ጡር ናት። ከተባለ ለአቶ ከበደ ላም.....ይባላል።

A. ክበድ B. ጥጉብ
C. ጥገት D. እርጉዝ

፵፱. መንፈስ ብሎ መንፈሳዊ ቢል ከየትኛው የቃል ክፍል ወደየትኛው የቃል ክፍል የተቀየረ ነው?

A. ከስም ወደ ቅጽል B. ከስም ወደ ግስ
C. ከቅጽል ወደ ስም D. ከስም ወደ ተውሳከ ግስ

፶. "ሰው ከሶኛል አሉ ቆሞ አደባባይ
እውነት ነውር ሆኖ ሊያስቀጣኝ ነው ወይ?" በዚህ ቅኔ ውስጥ ያለው ወርቅ የትኛው ነው?

A. እውነትም ከጥፋት ተቆጥሮ ያስቀጣል ወይ? B. የሠራሁት በእርግጥ ነውር ነበር ወይ?
C. ሰው በየመሥሪያ ቤቱ ይከሰኛል። D. የሠራሁት ሥራ ሊያስቀጣኝ ይችላል ወይ?

፶፩. "አዳራሹ ሰፊ ቤቱ አልጠበባችሁ
በተራ በተራ ምነው መግባታችሁ" በዚህ ቅኔ ውስጥ ያለው ሕብረቃል የትኛው ነው?

A. በተራ በተራ B. አዳራሹ ሰፊ
C. ምነው መግባታችሁ D. አልጠበባችሁ

፶፪. ከሚከተሉት ውስጥ በሀቅ ላይ የተገነባው ዓረፍተነገር የትኛው ነው?

A. የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉም ስጋ ወዳድ ነው።
B. ሰዎች ሁሉ በአንድ ጊዜ ሁለት ነገሮችን ማዳመጥ ይችላሉ።
C. የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንበብና መጻፍ ይችላል።
D. ኤች አይቪ ኤድስ በደም ንክክኪ ይተላለፋል ።

፶፫. በተገብሯዊ ግስ የተዋቀረ ዓረፍተ ነገር የባለቤት የተሳቢና የግስ አወቃቀሩ የቱን ሊከተል ይችላል?

A. ባለቤት፣ ተሳቢ፣ ግስ B. ተሳቢ፣ ባለቤት፣ ግስ
C. ተሳቢ፣ ግስ ፣ባለቤት D. ግስ ፣ባለቤት ፣ተሳቢ

፶፬. ከሚከተሉት ውስጥ ከግጥም ባህሪያት የማይመደበው የትኛው ነው?

A. ቁጥብነት B. ምናባዊነት
C. ወንጋራነት D. ተለዋዋጭነት

፶፭. ከግጥም ዓይነቶች ውስጥ ምጣኔው ስድስት በስድስት የግጥም አይነትየ የትኛው ነው?

A. የወል ቤት B. ሰንጎ መገን
C. ቡሄ በሉ ቤት D. የጸጋዬ ቤት

መመሪያ ሦስት፦ ከተራ ቁጥር ፶፯ እስከ ፷ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ግጥም ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ግጥሙን በጥሞና በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ።

ግጥም

መከራ ተረግዛ ተወልዶ ችግር፣
ስቃይ ተሞሽራ ሲዘፈን ባገር፣
ሀዘን ስትዘፍን አታሞ ስትመታ፣
ድህነት ሲሸልል እየነፋ እምቢልታ፣
ረሀብ ሲያቅራራ በጣለው ሰለባ፣
ቀጠና ደረሰ ድምጹ.....።
ቡትትም አጊጣ ከድሪቶ ጋራ፣
ዝተትና ማቅም ሆኖ በየተራ፣
መጡ ከእኔ ዘንድ አብረውኝ ሊውሉ፣
ተስማምተው ደረሱ እየተባበሩ።

፶፯. ከላይ የቀረበው ግጥም ስንት ስንኞችን ይዟል?

A. አስራ ሦስት　　B. አስር
C. ዘጠኝ　　D. ስምንት

፶፯. በግጥሙ ስድስተኛ መስመር ላይ ያለውን ባዶ ቦታ ሊያሟላ የሚችል የትኛው አማራጭ ነው?

A. እየጮኸ　　B. እያባባ
C. እያስተጋባ　　D. እየረበሸ

፶፰. የአራተኛው ስንኝ መድረሻ ሐረግ መነሻ ቃል የሆነው የቱ ነው?

A. አታሞ　　B. ስትመታ
C. ድህነት　　D. እየነፋ

፶፱. በግጥሙ ውስጥ በራብዕ ፊደል የሚጨርሱ ስንት ስንኞች ይገኛሉ?

A. አራት　　B. ስድስት
C. አምስት　　D. ስምንት

፷. "ሀዘን ስትዘፍን" የሚለው ሐረግ በምን አይነት ዘይቤ የቀረበ ነው ?

A. ግነት　　B. ተለዋዋጭ
C. ሰውኛ　　D. አነጻጻሪ